# ለቀጣይ ተግባር - የውይይት መነሻ ጥያቄዎች

1. ስለ ፖለቲካችንና የፓርቲዎች ተባብሮ መስራት ጥረት ከሁለት ድፍን ዓመታት በፊት እንዲህ ተብሎ ነበር -- ዛሬስ የት ደርሰናል??
2. በስም የተጠቀሱት--መድረክ፣መኢአድ፣አንድነት፣ሰማያዊ፣….እንዴት ናቸው??
3. ይህ ጽሁፍ ቀርቦ የነበረው --ኢዴፓ፣ ኢራፓና መኢአድ በቅንጅት/ትብብር ለመስራት የጀመሩትን ጥረት እንዲያግዝ ነበር -- ጥረቱ የት ደረሰ??
4. ከዚያ በኋላ የ16ቱ ‘ጥምረት’ የሚለው ጥረት የት ደረሰ??
5. ዛሬ አገራችንና ህዝባችን በተሻለ ወይስ በከፋ/የባሰ ደረጃ ላይ ናቸው፣??
6. ፖለቲከኞች፣ፓርቲዎችና የፓርቲ አመራሮች ከበሽታው ተፈውሰዋል ወይስ ጸንቶባቸዋል??
7. በቀጣይ ምን ይደረግ??

<u>በ2007 የተቃውሞው ጎራ የጋራ እንቅስቃሴ ቅኝት</u>
<u>ቀጣዩ በንስኃና ሱባኤ ማለፍ ያለበት የትብብር መንገድ //</u>

‹‹2007 ዓመቱ እንዴት አለፈ›› በሚል ጳጉሜ 1/07 በመኢአድ ወጣቶች በተዘጋጀ ፕሮግራም የቀረበ የውይይት መነሻ ኃሳብ ›› ---- ከግርማ በቀለ ፤

መቼም በዛሬው ዕለት በዚህ ቦታ ተገኝቼ ያሳለፍነውን ዓመት ወደኋላ ለመቃኘትና የቀጣዩን አቅጣጫ ለማመላከት በሚያስችል ውይይት ላይ ኃሳቤን ለማካፈል የተሰጠኝ ዕድል ለእኔ መታደል ነው፡፡ በውስጤ የሚብላላውንና በተደጋጋሚ በማኅበራዊ ሚዲያ ስጮህ የነበረውን ከእናንተ ጋር በግንባር ተገናኝቼ መወያየት መቻል ታላቅ መልካም አጋጣሚ ነውና ይህን መድረክ ላዘጋጃችሁና ዕድሉን ለሰጣችሁን የላቀ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ በዚህ ውይይት ለመሳተፍ የመለያየቱን አጥር ጥሳችሁ ለተገኛችሁ የሌሎች ፓርቲ አመራሮች የተለየ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ ውድ ጊዜአችሁን ሰውታችሁ የተገኛችሁ የጉዳዩ ባለቤቶች ሁሉ እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡

ወደ ርዕሰ ጉዳዬ ከመግባቴ በፊት እዚህ እንድገኝና ሃሳቤን እንዳካፍል ጥሪው ሲደርሰኝ በመጀመሪያ ወደ አዕምሮዬ የመጣው ኃሳብ የዚህ ውይይት አካል ነውና ገልጬ እንዳልፍ ይፈቀድልኝ፡፡መኢአድ በተለያዩ ቡድኖች በተከፋፈለበትና ‹‹አንዱ›› ወገን ባዘጋጀው መድረክ መገኘት ሌላውን ወገን የሚያስከፋና ለበለጠ መለያየት ቤንዚን ማቀበል ይሆን? የሚል ነበር፡፡ በእውነቱ በዚህ ዓይነቱ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር እንኳን መኢአድ -ኢህአዴግስ መድረክ ቢያዘጋጅ ለመገኘት ይህ ዓይነቱ ጥያቄ መነሳት/መታሰብ ነበረበት፣ ኃሳቡስ ከምን የመጣ ነው፣ ምን ያመለክታል ? ለእኔ ያለንበትን መከፋፈል፣ በመከፋፈላችን የተከተለውን ሽኩቻ፣ መፈራረጅና ፍራቻ፣ ከነዚህ የመነጨውን አላስፈላጊ ጥንቃቄ ፣ በአጠቃላይም መከፋፈላችን ተቀራርቦ ለመነጋገር/መወያየት እንኳ ዕድሉን የቱን ያህል እንዳጠበበ ነው ያስገነዘበኝ፡፡ እንግዲህ ራሴን እንደ የለውጥ ኃይልና በግል የሁሉም ወገን ወዳጅና በለውጥ ትግሉ ትክክለኛ ለምለው ኃሳብ አቀንቃኝና ጠበቃ ፣ የአገራዊ የጋራ ዓላማ አራማጅ ነኝ ብዬ ስለማምን ፣ ከአገራዊ ዓላማው የሚበልጥብኝ ቅንጣት ታክል የግል ስልጣንና ዝና ፍላጎት እንደሌለኝ እተማመናለሁና በዚህ መድረክ መገኘትና ኃሳቤን ማካፈል እንኳን ትናንት አብረው ሲሰሩ ለነበሩ ቡድኖች ፣ ለህወኃትም ቢሆን እንደ አገርና ህዝብ ለሁላችንም ጠቃሚ ነውና መልካም አጋጣሚ እንጂ የሚያሳስብ ሥጋት አይደለም ፤ ዋናው የመልዕክቱ ይዘት በግለሰቦች ላይ የማያተኩርና ለአገራዊ ዓላማው አስተዋጽኦ የመሆኑ ጉዳይ ነው ከሚል ውሳኔ በመድረስ ነው እዚህ የተገኘሁት፡፡ ይህ ውሳኔዬ ከላይ ላነሳሁት የመፈራረጅ… ሥጋት የተሟላ መልስ እንደማይሆን፣ እንደማያስቀረው፣ አኩርፈው የቀሩ እንደሚኖሩና በዚህ ጉዳይ ብዙ ሊባል እንደሚችልም አውቃለሁ፡፡ ብዙም አያሳስበኝምና ወደ ርዕሳችን እንግባ፡፡

እንግዲህ በእኔ ግንዛቤ 2007 ዓ.ም በዲሞክራቲክ የለውጥ ኃይል ጎራው (ኢህአዴግ ስሪቶችና ዳረጎት ተቀባዮች ሲቀሩ የተከፋፈሉትንና የተበታተኑትን ጭምር) በዋነኛነት የሚጠቀሰው እንቅስቃሴ ለረጅም ጊዜ ከህዝብ ይቀርብ የነበረውን የተባብራችሁ ምሩን ወይም ‹‹ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ›› ጥያቄ ለመመለስ የተደረገው ጥረትና የጥረቱ እንደወትሮው ያለመሳካት ብቻም ሳይሆን ያልተገመተ/ያልተጠበቀ ወይም ከተጠበቀው ተቃራኒ ውጤት አስከትሎ ማለፉ ነው፡፡ትንሽ አፍታተን እንመልከተው፡፡

በእርግጥ በዲሞክራቲክ የለውጥ ኃይል ጎራው የመተባበርና አብሮ የመሥራት ጥረት ዕድሜው ህወኃት (ኢህአዴግ የማልለው በዕውቀት ነው፣ የሌሎቹ ሚና ከአጃቢነት ያለፈ አይደለምና) ስልጣን ከተቆናጠጠበት

ጊዜ ይበልጣል፣(‹‹ኢዴኃቅ››ን ያስተውሏል)፡፡ በህወኃት ዘመንም ከ1984ቱ ደቡብ ኅብረት (23 ዓመታት) ቀጥሎ ካለው ከ1986 የግዮን የሰላምና ዕርቅ ጉባኤ ተነስተን ብንቆጥር እንኳ 21 ዓመታት አልፈዋል፡፡ በነዚህ 21 ዓመታት በኅብረት፣በቅንጅት፣ ትብብር ፣ግንባር አልፎም ውህደት ስም መዋቅራዊና መዋቅራዊ ያልሆኑ በዚህ መድረክ ቆጥረን የማንዘልቃቸው ያልተሳኩ/ የከሸፉ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡ ከ2005 አስቀድሞ ከተሞከሩት ከዋና ዋናዎቹ ኢተፖዲኅ፣ ትዲኢ፣ኢዴኃኅ/ኅብረት፣ ቅንጅትና መድረክን ጠቅሰን እንለፍ፡፡ እንደአጋጣሚ ሆኖ ዋና ዋና በሚባሉት አብዛኛዎቹ በአመራር ደረጃ ተሳታፊ ነበርኩና ይህን መድረክ የ ‹‹ክሽፈት ልምድ›› ማካፈያ አድርጌ ነው የምወስደው፡፡ ለመማር ለፈቀደና ለመታረም ለተዘጋጀ ክሽፈትም ያስተምራል-- አዎን አንድ ፈላስፋ ውድቀትን ‹‹ ሰባት ጊዜ መውደቅ ሳይሆን ለስምንተኛ ጊዜ ለመነሳት ያለመዘጋጀት/ያለመፍቀድ›› ብሎ እንደገለጸው ነውና ፣ ለቀጣዩ ትግል መሪዎች በተለይም የመጪዋ ኢትዮጵያና ዘመን ዋነኛና ቀዳሚ ባለቤቶች ‹‹ወጣቶች›› ይህንኑ የክሽፈት ሂደትና ውጤቱን ለማካፈል ስለሆነ ለማይቀረው ለውጥ ለሚደረገው ህዝባዊ ትግል አንዳች አስተዋጽኦ እንደሚኖረው እምነቴ ነው፡፡ የዛሬው የውይይት መነሻ ኃሳቤ ግን ከፕሮግራሙ ዓላማ አንጻር የቅርብ ጊዜ የትብብር ሙከራዎች በተለይም ከምርጫ 2007 ጋር ተያያዥና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዲሞክራቲክ የለውጥ ኃይል ጎራ ‹‹ተስፋ ሰጪ›› የትብብር ጥረት የተጠነሰሰው በጥቅምት ወር 2005 በአዳማ ነበር፡፡ 33ት ፓርቲዎች ከምርጫ በፊት ‹‹የፖለቲካ ምህዳሩ እንዲስተካከል/እንዲሰፋ ›› በጋራ ጥያቄ /ፔቲሽን የተፈራረሙበት፡፡ ይህን ጅማሮ ተከትሎ የነበረውን መነሳሳት፣ የተደረጉ ጥረቶችና ውጤታቸውን ዘርዘር አድርገን እንመልከት፡፡

<u>የ33ቱ ትብብር</u> ፡-

ይህ በአዳማ የተጠነሰሰው የመተባበር እርሾ ጠንሳሾች ከምርጫ ጋር የተያያዙ 18 የጋራ ጥያቄዎችን በመለየት ለምርጫ ቦርድና ለመንግስት በማቅረብ እነዚህ እስካልተመለሱና የፖለቲካ ምህዳሩ ካልተስተካከለ በምርጫ መሳተፍ ከአጃቢነት ያለፈ ትርጉም የለውም፣ ኢ-ህገመንግስታዊነትን ማበረታታት ነው… የሚል የጋራ አቋም ወስደው እነዚህ ጥያቄዎች እንዲመለሱ በጋራ ቆመን መንግስትና ምርጫ ቦርድ ላይ በኅብረት ተጽዕኖ ለማሳረፍ በጋራ ተንቀሳቅሰናል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ግንኙነቱን ወደተሻለ ደረጃ ለማሳደግ ጥረት አድርገናል፡፡ በዚሁ ሂደት የባለጉዳዮቹ ቁጥር ወደ 24 ቀንሶ ቀሪዎቹ 24ቱ ስምምነት አድርገው **በዚህ ግቢ ውስጥ** ለህዝብ ‹‹የምስራች ›› አሰምተው እየተንቀሳቀሱ ባለበት በቅድሚያ ሰማያዊ አፈንግጦ፣በቀጣይም-- በመድረክ/ አንድነት ውዝግብና የውስጥ ሽኩቻ ( 12ቱን አራግፎ) ፣ እንዲሁም በህወኃት በምርጫ ቦርድ በኩል የሚዘረጋ ስውር እጅ (2ቱን ሀብአዴድ፣ ደንጣ ዱባሞ ተቀምቶ) ቁጥራቸው ወደ ዘጠኝ አሽቆልቁሎ ዳግም በዚሁ ግቢ ትብብርን ወልዶ/ተክቶ ‹‹33ቱ›› በ‹‹ክብር›› አረፈ፡፡ እነዚህ ስምምነት ፈራሚዎች በዕለቱ የተነሳነውን ፎቶ ስንመለከትና የገባነውን ቃል ሲናነብ ምን ይሰማን ይሆን ? ለመልሱ ይረዳን ዘንድ የዕለቱን ውሎ የዘገቡ ጋዜጦችን አፈላልገን እንመልከት፡፡ ተጠያቂነትን ከህወኃት መጠየቅ ---ወቼ ጉድ// በዚሁ የ33ቱ የጋራ አጭር ቆይታ የሽኩቻው መነሻ አንድነት አባሉ የሆነው መድረክን ጨምሮ አንድነት 33ቱን ለራሱ ፕሮፖጋንዳ ተጠቀመበት የሚል ነበር፡፡ የትብብሩን የጋራ ዓላማ ሳይጎዳና ከትብብሩ ዓላማ ሳይጋጭ እያንዳንዱ የትብብሩ አባል ትብብሩን የራሱ ገጽታ ለመገንባት ቢጠቀም ሌላውን ምን እንደሚጎዳ ማን ያስረዳን ይሆን? በዚህ መልክ ነው 33ቱ ያበቃለት፡፡

<u>የትብብር ለዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ/ትብብር/</u>

ከላይ እንደተጠቆመው ይህም የምስረታውን አዋጅ ምርጫ ቦርድ በተገኘበት ያወጀው በዚህ ግቢ ውስጥ ነው፡ ፡ ብዙም ሳይጓዝ የመኢአድ አመራር /መሪ በሥልጣን ጥያቄ ኩርፊያ የተከተለው ሴራ በምርጫ ቦርድ በተለይ በፈላጭ ቆራጩ አቶ ወንድሙ ጎላ በመታገዙ ማመልከቻው በአየር ላይ ቀረ፡፡ እስካሁንም ከአየር ላይ አልወረደም፡፡ የሚገርመው ለትብብሩ የዝምታ ሞት ቀዳሚ ተጠያቂው መኢአድ ከተመሳሳይ ‹‹ ትብብሩን መኢአድ ተጠቀመበት/ ለራሱ ፕሮፖጋንዳ አዋለው›› ሃሜት አለመትረፉ ነው፡፡

<u>የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር</u>

ከላይ በተገለጹት ጥረቶች ሂደት ያለፉ 5ት ፓርቲዎች (መኢአድ፣ ሰማያዊ፣ አንድነት፣ መድረክ እና ኦፌኮ) የእንግሊዝ ኤምባሲ ምሳ ግብዣ ላይ ተገናኝተው የጠነሱስት ነው፡፡ ይህንን ጥንስስ ከስብሰባው በወጡ ዕለት ዕድል እንስጠው የሚል ጥሪ ከመኢአድ ‹‹ የወቅቱ›› ፕሬዝዳንት ከላይ በተገለጸው ትብብር ስም ስልክ እንደተደወለልኝ ግራ ብጋባም የውይይትና የግንኙነት በሩን መዝጋት አስፈላጊ አይደለም በሚል እምነት ከሌሎች በመምከር ‹‹ ከአሁን በኋላ የሚጀመር ጥረት በጥናት ላይ የተመረኮዘ ካልሆነ እኛ አንገባበትም›› በሚል ያቀረብነው ኃሳብ ተቀባይነት አግኝቶ 14 ፓርቲዎች ‹‹ ለምን ደጋግመን ወደቅን?›› በሚለው ርዕስ ለወራት ተወያይተንና አጥንተን የጥናት ሪፖርታችንን አጽድቀነው የስምምነት ሰነድ አዘጋጀን፡፡ የግንኙነታችንን መጀመርና በየጊዜው የሚናከናውነውንና የደረስንበትን ለህዝብ ጆሮ እያደረስን

በተለመደው ‹‹ከወትሮው የተለየ በጥናት ላይ ተመስርተን ›› ለተባብራችሁ ምሩን ጥያቄኣችሁ ምላሽ ይዘንላችሁ መጣን ከበሮ ደለቅን፡፡ በእኛ ተስፋ ያልቆረጠው ህዝብም አደመጠን፣ ተስፋው የለመለመለት መስሎት ከአገር ውስጥና ከውጪ በተለያየ መንገድ ድጋፉን ገለጸ፡፡

በጅምሩ በመድረክና አንድነት መካከል የነበረው ውዝግብ አገረሸቶበት ሁለቱም (መድረክ በአንድ ወገን አንድነት በሌላው) አንዱን እንድናገል ቢሞክሩም ችግራቸውን በራሳቸው እንዲፈቱ መክረን ፣ምክራችንን ተቀብለው እስከ መጨረሻው አብረን ዘለቅን፡፡ በመካከሉ ግን በአንድነት የውስጥ-ለውስጥ የአመራር ለውጥ ሽኩቻ ተነስቶ ነበርና ከላይ ያዘጋጀናቸውንና ያጸደቅናቸውን ሰነዶች ከመፈራረማችን በፊት የአንድነት አመራር ‹‹በወጣት አመራር›› ተተካ ተባለ፡፡ በፊርማው ዕለት የመድረክ ተወካይ በፊርማው ቦታ ተገኝተው ከጅምሩ ያነሳነው ከአንድነት ጋር ያለው ጉዳይ በቅርብ ቀን በምናደርገው ጉባኤ እልባት ስለሚያገኝ ዛሬ ለመፈረም እንቸገራለን፣ እልባት እንደሰጠነው እንቀላቀላችኋለን፣ በሚል ፤ አዲሱ ወጣት የአንድነት መሪም ስብሰባው ላይ እያለን ደውለው ‹‹ የሥራ ክፍፍል ባለማድረጋችን እንጂ ከዚህ ስብስብ ውጪ አይደለንም፣ በቀጣዩ ስብሰባ ወስነን እንቀላቀላችኋለን፣ የሥራ ክፍፍል እንዳደረግን ተወካያችንን እናሳውቃለን›› በሚል ፊርማው ላይ ሳይገኙ ቀሩ፡፡ በዕለቱ የቀሩት 9ኝ ፓርቲዎች የጥናቱን ሰነድ እንደ ስምምነቱ አካል ተቀብለው የስምምነት ሰነዱን ፈርመው ‹‹ የ9ኙን ፓርቲዎች ትብብር›› መሰረቱ፣ አመራራቸውን መረጡ፣ የተለመደውን ‹‹የምስራች ›› ከህዝብ አደረሱ፡፡

አዲሱ ትብብር በአጭር ጊዜ ወደ ተግባር ገባ፣ ‹‹ ነጻነት ለፍትሃዊ ምርጫ›› በሚል መፈክር የተለያዩ አገር አቀፍ የተግባር ዕቅድ አውጥቶ እንቅስቃሴ ጀመረ፡፡ በዚህ ጉዞ ላይ እያለ እንደ አንድነት በመኢአድ ውስጥም የአመራር ሹም ሽር ተደረገ፡፡ አዲሱ አመራር ለትልቁ መኢአድ የተሰጠው ቦታ አልመጠነውምና አፈገፈገ፡፡ ገና ከጅምሩ በስልጣን ክፍፍሉ ደስተኛ ያልሆነው መድረክና የተወሰኑ አባላቱ ከዚህ ቀጥሎ ባለው እንቅስቃሴ መድረክና ትብብሩ እንደ ሁለት የተለያየ አደረጃጀት በእኩልነት እንሰራለን እንጂ በአባልነት አንሳተፍም ሲሉ ግልጽ የስልጣን ጥያቄ አቅርበው በመሪነት ያስጠኑት ጥናት ላይ የተጠቀሰው በሽታ እንዳገረሸባቸው አሳወቁ፣ ትብብሩ በሰማያዊ ተጠልፎ ለሰማያዊ ፕሮፖጋንዳ መጠቀሚያ ዋለ ክሳቸውን ይዘው መዞር ጀመሩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ ባለንበት ነው የምርጫ 2007 የጊዜ ሰሌዳ ይፋ የሆነው፡፡

በዚህ ጊዜ ሰማያዊ ለትብብሩ አባላት ሳያሳውቅ የራሱን የምርጫ ግብረ ኃይል ማቋቋሙን ይፋ አደረገ፡፡ በአባላት መካከል ቅሬታዎችና ጥያቄዎች ውስጥ ለውስጥ ይንሸራሸሩ ጀመር፡፡ ከዚህ አስቀድሞ በተደረገው የአዳር ሰልፍ ጥሪ ከ80 በላይ አመራር፣ አባላትና ደጋፊዎች ታስረው ቢፈቱም በቀጣይም የ ‹‹ ነጻነት ለፍትሃዊ ምርጫ›› እንቅስቃሴ አልተቋረጠም፡፡ የትብብሩም የአሰራርና አመራር ሥርዓት የመጀመሪያው ወር እንቅስቃሴ ሪፖርት ለማዕከላዊ ምክር ቤቱ ቀርቦ ውይይት ተደረገበት፣ ጸደቀ፡፡ ነገር ግን በዚህ የአሰራር ሥርዓት መሰረት ለመመራት ሳይቻል የዕጩ ማቅረቢያ ጊዜው በመድረሱ የትብብሩ አባላት ማን የት እና በምን መስፈርት ዕጩ ያቅርብ በሚለው ላይ ሳይመክሩ ሁሉም በየራሱ በተናጠል ዕጩውን አቀረበ፡፡ የጥናቱ አካል የነበሩት በ2005 የቀረቡት18 ጥያቄዎች ጉዳይ፣ የ‹‹ ነጻነት ለፍትሃዊ ምርጫ›› መፈክር፣ ስምምነቱና የትብብሩ ዓላማ ውኃ በላው፡ ተለመደው የተናጠል ሩጫ ቀጠለ፡፡ በዚህ አጋጣሚ በመኢአድና አንድነት ላይ ምርጫ ቦርድ የወሰደው እርምጃ ለ‹‹ ሰማያዊ›› መልካም አጋጣሚ የፈጠረ ስለመሰለው ሰማያዊ የተለመደውን የተናጠል ጉዞ አጠናክሮ በመቀጠሉ ከስራ አስፈጻሚው ውጪ ያሉ የትብብሩ አባላት ተበተኑ፡፡ እንደ ትብብር ከዚህ በኋላ የተገናኙበት የጋራ መድረክ የለም፡፡ በዚሁ መልክ ወደ ምርጫ ተገባ ፣ሁላችንም በምናውቀው መንገድ ተጠናቀቀ፡፡ ስለዚህ ትብብር በምርጫ 2007 በጋራ መስራት ይቅርና ስለ ምርጫው አልመከረም፡፡ በዚህ መልክ የ ‹‹9ኙ ፓርቲዎች ትብብር›› እንደ ቀደመው ‹‹ትብብር›› የጸጥታ ሞት ብይን ተላለፈበት፡፡ የሞት ፍርዱ መፈጸሙ አልተሰማም ፣ ይኑር/ይሙት አለየለትም፡፡

ከነዚህ ተሞክሮዎች የምንረዳው በየጊዜው የሚደረጉ ሙከራዎች በጋራ ለመስራት በሚደረሰው ስምምነት መሰረት በሰብሳቢነት ለሚመረጠው ወይም ለትብብሩ ቢሮ ለሚሰጠው ፓርቲ ፕሮፖጋንዳ ጥቅም ዋለ፣ የፓርቲ መሪዎች የአመራር /ሰብሳቢነት/ ቦታ አጣን በሚል የሚከሽፉ መሆኑንና ግንኙነታችን/ድርጊታችንም ‹‹ የማይተማመኑ ባልንጀሮች በየወንዙ ይማማላሉ›› መሆኑን ነው፡፡ ይህ ከሆነ መፍትሄው በጋራ አመራር ወይም የዙር ሰብሳቢነትና ከፓርቲዎች ቢሮ ውጪ ትብብሩ የራሱን ጽ/ቤት እንዲያቋቁም ማድረግ መፍትሄ ሊሆን ይችል ይሆን?

<u>ከነዚህ ጎን ለጎን ሲደረግ የነበረው የፓርቲዎች የውህደት ጥረትና ውጤቱ፤</u>

ከላይ ከተጠቆመው 2005 ምርጫ ወዲህ ባለው ጊዜ ከትብብር ጥረቶች ጎን ለጎን የፓርቲዎች ውህደት ተነግረዋል፣ጥረቶች ተደርገዋል፤ አስደማሚ፣ አነጋጋሪና አሳዛኝ ዋጋ አስከፍለው አንዳቸውም ሳይሳኩ ቀርቷል፡፡ እንዴትና ለምኑን በወፍ በረር እንመልከት፡፡

**በመድረክ አባል ፓርቲዎች መካከል**

በመድረክ ፓርቲዎች መካከል ውህደት እንዲፈጸም ከውስጥና ከውጪ ጥያቄ መቅረብ የጀመረው ከሁሉ በፊት ነው ማለት ይቻላል ፡፡ ሆኖም አይደለም ውህደት በግንባርም ደረጃ ለመቀጠል ያለው ግንኙነት በርካታ ጥያቄዎችን አርግዞ በተለይም በአንድነትና በሌሎቹ መካከል የነበረው ግንኙነት መፍትሄ የማያገኝ ቅርቃር ውስጥ መግባቱ የአደባባይ ምስጢር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ያልጠራ ግንኙነት እየተሸፋፈነ የጊዜ ፈንጂ ሆኖ ተቀብሮ ቆይቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የአንድነት የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ከባለራዕይ ወጣቶች ወደ አንድነት አመራር መምጣት ተከትሎ ለመፈንዳት ጊዜ አልወሰደበትም ፡፡ ፍትጊያው አደባባይ ወጣ፣ እንካ-ሰላምታው ከሚያስተዛዝብ ደረጃ ደረሰ፡፡ ይሄው ሁኔታ የአንድነትን ፕሬዝዳንት የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ከፓርቲ ፖለቲካ የማግለል ውሳኔ ላይ ማድረሱ ግልጽ ነው፡፡ በመቀጠልም የአንድነትና መድረክ ግንኙነት በመተዳደሪያ ደንብና የአሰራር ስርዓት ታስሮ ከላይ እንደገለጽነው እስከ ‹‹የ9ኙ ትብብር ምስረታ›› ዘለቀ እንጂ ከማይታረቁበት ደረጃ የደረሰው አስቀድሞ ነበር፡፡ ከአንድነት ውጪ ባሉት መካከልም እውን ሳይሆን ዛሬ ላይ ደርሷል ፣ ለምን አልተዋሃዱምን እንኳን ህዝብ-መድረክ እንደ ግንባርና የአባል ፓርቲዎቹ አመራሮች ግልጽና አሳማኝ መልስ ሊሰጡ አልቻሉም፡፡ ዛሬም ችግሩ እንደተሸፈነና እንደተዳፈነ አለ ብሎ ከግምት በላይ ተራምዶ መናገር ይቻላል፡፡

**መኢአድ/አንድነት**

ይህ ከተጠነሰሰበት ጊዜ አንጻር ረጅም ዕድሜ አስቆጥሯል ቢባልም አንድነት በመድረክ ግንኙነት ላይ በነበረው ጠንካራ እምነት ተጥሎ ቆይቶ ከላይ የገለጽነው የመድረክ/አንድነት ችግር ሲከሰት ከተጣለበት አፈሩን አራግፎ የተነሳ ግንኙነት ነው፡፡ በውህደት ግንኙነቱ መካከል በዋነኛነት የሥልጣን ክፍፍል ጉዳይ ረጅም ጊዜ ወስዶ ፣ አዋራ ሲያነሳ ቆይቶ፣ ለሽምግልና አስቸግሮ ፣ ይህንኑ ተከትሎ በአንድነት ውስጥ ከአገር አልፎ ባህር የተሻገረ የ‹‹ኩዴታ›› ማዕበል አንስቶ ዓመት ያልሞላውን ፕሬዝዳንቱን ከፖለቲካው ሜዳ አባሮ፣ በመጨረሻም ሁለቱንም ለመከፋፈል ለምርጫ ቦርድ በሩን በርግዶ አንድነትን ጨርሶ ሲበላ በመኢአድ ውስጥም እስከዛሬ የዘለቀ ያለመተማመን ዘር ዘርቶ እያፈራረጀ፣ እያወነጃጀለና እያካሰሰ ዘልቋል፡፡ ቀጣዩን አብረን የምናየው ይሆናል፡፡

**መኢአድ/አንድነት/‹‹ትብብር››**

ይህ በዋነኛነት የውህደቱን መሰረት ለማስፋት በሌላ በኩል በመኢአድና አንድነት መካከል በተጀመረው የውህደት ሂደት ላይ ላጋጠመው ችግር መፍትሄ እንዲሆን፣ በሚል ዓላማ የተጀመረ ጥረት፣ ከአንድነት በኩል ሙሉ ድጋፍ ቢያገኝም የወቅቱ የመኢአድ ፕሬዝዳንትና በ‹‹ኩዴታ›› ሊመጣ ያቀደው የአንድነት ‹‹ወጣት አመራር›› መካከል ዛሬ በስደት የሚገኘው በመጨረሻው የአንድነት ማዕከላዊ ም/ቤት ምክትል ሰብሳቢ አስተባባሪነት (እማኝ ባለበት በግንባር ደጋግሜ ነግሬዋለሁ) በተደረሰ ስውር የጓሮ ስምምነትና በመኢአድ ፕሬዝዳንት ፈጻሚነት በአጭሩ የተቀጨ ጥረት ነው፡፡

**አንድነት/‹‹ትብብር››**

ይህ የአንድነት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ከመኢአድ ጋር የተጀመረው ስምምነት ጥያቄ ውስጥ መውደቁን ወይም ያለመሳካቱን በመገንዘብ ተጀምሮ ሁለቱም ኮሚቴዎች ሰይመው ተደጋጋሚ ውይይት ካደረጉና በመሰረታዊ ጉዳዮች ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ ከላይ የተገለጸው የአንድነት ማዕከላዊ ም/ቤት የመጨረሻው ምክትል ሰብሳቢ አስተባባሪነት በሚመራው የ‹‹ወጣት አመራር›› አዋላጅ የኩዴታ ቡድን በመንገድ ላይ በተጻፈ የመኢአድ ደብዳቤ የተጨናገፈ ጥረት ነው፡፡

ከነዚህ ጥረቶች ያለመሳካት ጀርባ ያለው ዋናው ጥያቄ የፓርቲ አመራሮች የስልጣን ጥያቄ መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም፡፡ የሚያሳዝነው ለህዝብ ከምንነግረው፣ በፓርቲያችን ከምንወስነው በላይ በፓርቲ ጥቅም ማስከበር ስም መሪዎች ለስልጣን ያለንን የተደበቀ ፍላጎት ነው፡፡ እንኳን ህወኃትን በመታገል ላይ ባለ ድርጅት ቀርቶ ‹‹አሸንፈን›› ለሥልጣን ብንበቃ ለዚህ ችግራችን መፍትሄ እንዲሆን አገሪቷ ስንት ፕሬዝዳንትና ጠቅላይ ሚንስትር ይኖራት ይሆን? የሚል የጅል ጥያቄ አንስቼ አልፈዋለሁ፡፡
ግን እዚህ ላይ በሁሉም ፓርቲና የፓርቲዎች ስብስብ በሚመራ እንቅስቃሴ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የሚደርሰውና የሚከፈለው ዋጋ አለመቅረቱ፣ ዛሬም በየወህኒውና በየማጎሪያው ሥቃይ የሚቀበሉ መኖራቸውን አስታውሰን ማለፍ ግድ ይላል፡፡

**ከላይ ከተነሱት ጥያቄዎችና ከተገለጹት ጥረቶች አንጻር የምርጫ 2007 ትዕይንት፤**

እዚህ ላይ በጣም አስገራሚ የፓርቲዎችን የምርጫ ተሳትፎ አቋምና እንቅስቃሴ እንመለከታለን ፡፡ **እነዚህም ፡-**

አንድነት ለ33ቱ ቢሮ በመስጠቱና የ33ቱ መሪም በመድረክ ውክልና የአንድነት አመራር በመሆናቸው ሲታማበት በነበረው በ33ቱ የተዘጋጀው 18 ጥያቄ ባልተመለሰበት ፣ የ‹‹9ኙ ትብብር›› ጥናትና ስምምነት ከላይ በተገለጸው መንገድ በተሳተፈበትና ባጸደቀበት፣ በወቅቱም ‹‹ነጻነት ለፍትሃዊ ምርጫ›› በህዝብ ተቀባይነት ባገኘበት ሁኔታ ውስጥ እንደምን የ‹‹ወጣቱ አመራር›› በምርጫው ‹‹ ያለቅድመ ሁኔታ ለመሳተፍ ›› መወሰኑ ነው፡፡ ከምርጫ ቦርድ ለአዲሱ ‹‹የወጣት አመራር›› ዕውቅና ለማግኘት የተደረገ ጥረት ከሆነም ከጊዜ ጋር የሚታይ ይሆናል፣በውጤቱ ግን ሙከራው ባለመሳካቱ አንድነት ለምርጫው አልደረሰም፤መፍረሱ ግን ሰማያዊን በማሳበጥ በትግሉ ላይ ተጨማሪ አሉታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል ፡፡

ሰማያዊ በመጨረሻ ሰዓት የአንድነት ፓርቲ መፍረስ በፈጠረለት መልካም አጋጣሚና ከትብብሩ ጋር በመስራቱ ካገኘው ተጨማሪ ተቀባይነት የታገዘው  ያለ ምክክር የተቋቋመው ግብረኃይል- ‹‹ትብብሩን ›› አባላት ባለማስተባበሩ ሊቀመንበሩ በ‹‹ዕጣ›› የወደቁት  በተናጠል አንድ ዕጩ ብቻ ያቀረበ የትብብሩ አባል ፓርቲ ጥሎአቸው ነው፡፡

መድረክ- በመጨረሻው ሰዓት ባደረገው የምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻ  ኦሮሚያና ደቡብ በህዝብ የራስ ተነሳሽነት የተገኘው ድጋፍ በድርጅታዊ ሥራ የተገኘ ያህልና በህወኃት ደህንነት የተሰራጨው ለተቃዋሚዎች የተወሰነ ወንበር ይለቃል የሃሰት ፕሮፖጋንዳ  አቋሙን አስቶት  አመራሩን ባልተለመደ ሁኔታ ‹‹የምርጫው ውጤት እንደ 2002 ከሆነ ከፖለቲካው ጡረታ እወጣለሁ›› እስከ ማለት አድርሷል፡፡ ከምርጫው ውጤት በኋላ የተሰማው ከወትሮው የተለየ ጠንካራ አቋምም ይህንኑ ያሳያል፡፡

መኢአድ -- ባልታሰበ ሁኔታ ስልጣን እጁ የገባው የወቅቱ የመኢአድ አመራር በፓርቲው ውስጥ ከተከሰተው መከፋፈል ባሻገር በአዲሱ አመራር ውስጥም ወደ ምርጫው እንግባ/አንግባ ጥያቄ የፈጠረው ክፍተትና መከፋፈል የከፊል አዲሱ አመራር አባላት አንሳተፍም /ራሳችን አግለናል አቋም የመኢአድ መሪ ትናንት ያልተባበሯቸውን ሌሎች ፓርቲዎች በአንግባ ላይ የጋራ አቋም እንዲወስዱ  ከምርጫ ቅስቀሳው በላይ ዘመቻ ቢያደርጉም አልተሳካም፡፡

ከላይ የተነሱት 18 ጥያቄዎች ባልተመለሱበት፣ ‹‹ነጻነት ለፍትሃዊ ምርጫ›› መፈክር መንገድ ላይ ተጥሎ የተገባበት ምርጫ ውጤትን እንኳን ህዝቡ የእነርሱ አባላትም ለመቀበል የተቸገሩበት  መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በእኛ በኩል ግን    ህዝብን ካልናቅን አስተማማኝ አማራጭ ባላቀረብንለት ህዝብ መርጦናል ማለትና ህወኃት አልተመረጠም፣ አጭበረበረ በሚል ብቻ ችግራችን ወደ ውጪ በመግፋት ማጠቃለል በሽታውን መደበቅ ነው፡፡ለቀጣይም መድሃኒት አያስገኝም፡፡  የምርጫውን  ሂደትና ውጤት  በሚመለከት የሆነው በ18ቱ ጥያቄዎች የተነሱት ጉዳዮች በግልጽ ያስቀመጡትና እነዚህ ችግሮች በተባበሰ ሁኔታ መቀጠላቸው ብዙ አከራካሪ አይደለም፡፡ መመለስ ያለበት ዋናውና አቢዩ  ጥያቄ ዲሞክራቲክ ኃይሎች እነዚህ ጥያቄዎች ባልተመለሱበት ወይም እነዚህን ችግሮች ለመቋቋምና ለመመከት ባልተዘጋጀንበት በምርጫው መሳተፍ ነበረብን ፣ያውም በተናጠልና እርስ በርስ እየተፎካከሩ?

ከእነዚህ ተደጋጋሚ ክሽፈቶች  መጨበጥ የሚቻለው አጠቃላይ ግንዛቤ የተቃውሞ ጎራ ‹‹ዲሞክራቲክ›› ፓርቲዎችና አመራራቸው በየጊዜው የተስማሙበትንና የሚፈራረሙበትን አያነቡም/አያውቁም ወይም ነገ በታሪክና በትውልድ የሚያስጠይቅ መሆኑን አይረዱም/ የህዝብ ንቀት/፣ ስለአገርና ህዝብ በአደባባይ የሚናገሩት  ከፓርቲ ፍላጎትና ጥቅም ቂምብል ውስጥ ባለው የእነርሱን የግል መሪነት፣ ክብርና ዝና፣ ጥቅም…እስካላረጋገጠ ጉዳያቸው አይደለም…. ማለት ያስችላል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ዛሬም በ14ቱ ጥናት የአመራሮችና የፓርቲዎች ችግር ተብለው ለተዘረዘሩት መፍትሄ ሳያበጁ  ከሌላው መተባበር ቀርቶ በራሳቸው ውስጥ ያለውን ችግር ሳይፈቱ በዚያው ተመሳሳይ መንገድ ለመቀጠል የሚታየው መንገታገት ነው፡፡

ይህን ሁሉ ካልኩ በኋላ ግን ዛሬም በአገሪቱ ያለው ተጨባጭ እውነታ ‹‹ለውጥ አይቀሬ›› መሆኑን ያመላክታል ፡፡ ዋናው ጥያቄ ‹‹ለውጡ›› በማን፣ እንዴት፣ …. ሊመጣ እና በተረጋጋና ሰላማዊ መንገድ ሊከናወን ይችላል ነው?

ለእኔ ማዕከላዊው ጉዳይ/ነጥብ በየቱም ጊዜ ያለፈውና ያለው ‹‹ባለኃይል›› ስርዓት ወንድሙን እያሰረ ፣ እያሰቃዬ፣ እየወነጀለ፣…. እንዲሁም እየገደለ በዚህች አገር በተረጋጋና መተማመን ባለው  የሥልጣን ሽግግር ዘላቂ ሰላምና ልማት ሊያመጣ አልቻለም፡፡ አይችልም፡፡ ወንድሙን በማሰቃየቱ የጀግንነት ክብር ሳይሆን ፍርኃትና መሸማቀቅ ነው የተጎናጸፈው፣ድንገት ደራሹ አይቀሬው ለውጥ ሲመጣ ራሱን ለተለመደው

ስደት፣ ወይም መቃብር አዘጋጀ እንጂ በአገሩ በክብር የሚያርፍበትን ቦታ አላዘጋጀም፡፡-የእኔ ጥያቄ ይህ እስከመቼ ይቀጥል ነው?

የተቃውሞ ጎራውም ከመተማመን/መካካድ፣ ከመተባበር/መለያየት፣..... ምርጫችን ሁሌም የጥፋት፣ ውድቀትና ክሽፈት በመሆኑ ደጋግመን ወድቅን፡፡ ግን አልተነሳንም፡፡ ለመነሳት ከምናደርገው ጥረት በላይ በተለመደው የክሽፈት መንገድ ለመቀጠል ያለንን ፍላጎት ማሳያዎች ጎልተው ይታያሉ፡፡
በሁለቱም ጎራ ያለን ፖለቲከኞች ፖለቲካን ከመዋሸትና ፕሮፖጋንዳ አጋብተን ዛሬም የማንተገብረውን ቃል እየገባን ድክመታችንን በፕሮፖጋንዳ እንሸፍናለን....ለምን? ብለን ለመጠየቅ ድፍረቱ ይጎድለናል፣ በሥልጣን ላይ ስንሆን ኃይላችን ዘላለማዊና የማይደፈር ይመስለናል፣ ከትናንት ለመማር አዕምሮአችን ይዘጋል፣ የአደባባዩን ለመስማት ጆሮአችን ይደፈናል፣ግልጽና የጠራውን ለማየት ዓይናችን ይጋረዳል....አገር አራቁተን፣ ለአገር ተረካቢ ልጆቻችን አሳፋር ታሪክ አቆይተን አይቀሬ አይሞቱ ሞት መሞትን ምርጫችን ያደረግን ይመስላል፡፡

የእኔ ሰበካና ማሳሰቢያ የሁለቱም ካምፕ ፖለቲከኞች ካለፈው እንድንማር ነው፡፡መነሻዬም ከዚህ በፊት የደረስንበት ‹‹ ለአገራችን ውስብስብ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ገዢውን ፓርቲ/ ህወኃትን ጨምሮ ማንም ብቸኛ ኃይል በተናጠል ዘላቂ መፍትሄ አያመጣም›› የሚለው መደምደሚያ ነው፡፡ በቅድሚያና በተለይ በሥልጣን ላይ ያለው ህወኃት በተለመደው መንገድ በክህደት፣ በአፈና፣በማጭበርበርና በመከፋፈል፣..... በጥድፊያ እየጋለበ እየመጣ ያለውን ለውጥ አይቀለብሰውም፡፡ ራሱን ከውድቀት ሊከላከልና ሥልጣኑን እስከወዲያኛው ሊያቆይ አይቻለውም፣ ወይም በሩቅና በቅርብ ደጋግመን ካየነው የአምባገነኖች የውርደት ፍጻሜ አይተርፍም፡፡ የተቃዋሚ ጎራውም ከመከፋፈል፣ ከመፈራረጅና፣ከመወነጃጀል ሳይላቀቅ፣ በራሱ ውስጥ መተማማንና ኅብረት ሳይፈጥር ... ህወኃት ካልጠፋ/ካልወደመ እንቅልፍ የለኝም በሚል የመቅበር/መጠፋፋት አግላይ ፖለቲካ አገራዊ ዘላቂ ሰላምና ልማት፣ፍትህና ዲሞክራሲ፣ ሉአላዊነትንና የህግ የበላይነትን ....እውን አያደርግም፡፡ ስለሆነም ለመፍትሄው ልዩነቶቻችን እንደተጠበቁ ሆነው እንደ ‹‹አንድ አገርና ህዝብ›› ለዚሁ በጋራ/ትብብር በተግባር እንቆም ዘንድ ለእስከዛሬው ክሽፈታችን ሁላችንም በድርሻችን ልክ በህዝብ ፊት የንሥኃ ቃላችንን ሰጥተን ህዝቡን ይቅርታ ጠይቀን የፍቅር ሱባኤ ገብተን እንሞክር ፤ ይህም በሌላ አገላለጽ በብሄራዊ ውይይት ብሄራዊ መግባባት ላይ ደርሰን ዕርቅ በማውረድ የሚመሰረት አካታች የሽግግር መንግስት ነው፡፡ ለዚህ ግን ሱባኤና ንስኃው ማለትም ውይይቱና በጋራ አገራዊ አጀንዳ ላይ ስምምነትና መግባባት ላይ መድረሱ በቅድሚያ ከተቃውሞ ጎራው የሚጠበቅ ሲሆን ለዚህ ደግሞ የፓርቲዎች በተለይም የፓርቲ መሪዎችን የፖለቲካ ቁርጠኝነትና መስዋዕትነታቸው ለአገርና ህዝብ መሆኑን በሚነግሩን ልክ ሆኖ የመገኘት ውሳኔን ይጠይቃል፡፡ይህ የፖለታካ ቁርጠኝነትና የሚሉትን ሆኖ መገኘት ውሳኔ ከምንለው አንጻር አይበዛብንም፡፡

ከዚህ ውጪ ከየአቅጣጫው እንደ ደራሽውኃ እየተምዘገዘገ እየመጣ ያለውን የለውጥ ባቡር ማንም አያቆመውም፣ ሊያደርስ የሚችለውን ጥፋትና ውድመት ማንም አይቆጣጠረውም፣አይታደገንምም፡፡ የአንበሳ ድርሻው የህወኃት ቢሆንም ማንም ፓርቲና ፖለቲከኛ ነኝ ባይ አልፎም አገሪቱ ያፈራቺው ልህቅ ከታሪክና ትውልድ ፍርድ አያመልጥም፡፡ ልብ ያለው ልብ ይበል፡፡

በዚህ የውይይት ኃሳብ ዓላማዬ ለአገሬና ህዝቧ የሚበጀውን ኃሳብ ማቅረብ፣ከትናንቱ እንድንማርና በጋራ ጉዳያቸን ላይ በአንድነት እንድንቆም በመረጃና ማስረጃ በማስደገፍ መስበክና ማሳሰብ እንጂ ማንንም በግል ለማስከፋትም ሆነ ጣት ለመጠንቋቆል አይደለም፡፡ ነገር ግን ማንም ለ‹‹ክሽፈታችን›› ባዋጣው ልክ ቢከፋ ብዬ ቅንጣት አልተጠነቀቅሁም፤ አላደረግሁም ወይም አልከሸፍንም የሚል ካለ እንደእኔው ኃሳቡን በመረጃና ማስረጃ አስደግፎ በግልጽ በወግና በስነምግባር መጻፍና መከራከር ይችላል፡፡ እዚህ ላይ ስማቸው ለተነሳ ወይም ከአገላለጹ ለሚታወቁ አሁን የነገርኳችሁን በግንባር የነገርኳቸው መሆኑን እንድትረዱልኝና በማንም ላይ ከጀርባ የሚሸርበው ሴራ ያለመኖሩን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ፡፡

ይህን ሁሉ ስንል ስለክሽፈታችን በእጃችን ያለውን መረጃና ማስረጃ ሁሉ አንናገርም፣ ለጊዜና ታሪክ የምናቆየው ይኖራል፡፡ ምክንያቱም እንደየሁኔታው የምነገርና የማይነገር መኖሩን ጠንቅቀን ስለምናውቅ ፣ ዛሬም ስለቀጣዩ ትግል ስለምንጨነቅና ስለምንጠነቀቅ፣ ሁሉንም መዘክዘክ ጉዳቱ ስለሚያመዝን - ለምንጠብቀው ትብብርና ዕርቅ ስለማይጠቅም ፣መቆየቱም ያን ያህል አይጎዳንም በሚል ነው፡፡::

እዚህ ጋ መታበይ አይሁንብኝና ስለራሴ በአደባባይ ተናግሬ ማብቃት እወዳለሁ፡፡ይሄውም ይህ ሁሉ ጩሄት ከፖለቲካ ስለሚገኝ ጥቅምና የተለየ ሥልጣን ፍላጎት ያለመሆኑንና እንዲያውም የተቃውሞው ጎራ በምፈልገው መንገድ ቢሄድ የፖለቲካ ‹‹ ጡረታ ›› ዛሬውኑ ለመውጣት ዝግጁ መሆኔን ማረጋገጥ ነው፡፡

በጥቅም ጉዳይም የእስከዛሬ 24 ዓመታት ትግል (ከከፈልኩት የሚለካና የማይለካ መስዋዕትነት) ውጪ የተንቀሳቀስኩት በራሴ ወጪና በፓርቲዬ ለሚደረገው እንቅስቃሴ ከኪሴ ከመደጎም ውጪ ከየቱም ፓርቲም ሆነ የፓርቲዎች ስብስብ በቋሚ ደመወዝ/ክፍያ ቀርቶ ለቀን ወጪ፣ ለስልክና ለትራንስፖርት  ቀይ ሳንቲም ያልተቀበልኩ መሆኔን ነው፡፡

በመጨረሻም የእስከዛሬው ጩሄታችን ሰሚ አጥቶ ከገባንበት የጥላቻና የዘር ፖለቲካ እና የግል ዝናና ጥቅም ፍለጋ እስር ቤት ወጥተን በአደባባይ በምንናገረው ቃል እንድንገኝ ባያደርገንም ፣ ‹‹በተቀበልነው›› የፖለቲካ ትርጉም ፊት የዋህና ጅል ሆነን ብንታይም ፣ የምንከተለው የክሽፈት ጎዳና እስካልተቀየረ ድረስ ከተለየ ውጤት አያደርሰንምና ለአገራችንና ህዝቧ ስንል እስከምንሰማ ጩሄታችንን አናቆምም ፡፡
**ፈጣሪ አገራችንና ህዝቧን ባርኮ ኢትዮጵያ በክብር ለዘላለም ትኑር//**

የመወያየ ጥያቄዎች ማጣቀሻ ዛሬስ? ይህ ከ3ዓመት ተኩል በፊት   /መጋቢት21/2005/ ከአንድነት ፓርቲ ልሳን /ፍኖተ-ነጻነት/ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ     ነበር፤
file://localhost/H:/.Trashes/OPDU%20Note/GIRMA%20for%20FINOTE%20N.htm.
የዛሬው እንግዳችን አቶ ግርማ በቀለ ይባላሉ ፡፡ አቶ ግርማ በቀለ በቅርቡ የትብብር ሠነድ የተፈራረሙት 33ቱ ፓርቲዎች ጊዜያዊ አስተባባሪ ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ እና የኦሞ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ህብረት /ኦህዴህ/የተባለ ፓርቲ ሊቀመንበር ናቸው፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡- ፔቲሽን ፈራሚ ፓርቲዎች አሁን በምን እንቅስቃሴ ላይ ናቸው?
አቶ ግርማ፡- የፔቲሽን ፊርማው ወደ ትብብር ሠነድ ከተሸጋገረ በኃላ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ የቀጣይ 6 ወራት ተግባር እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ትብብሩን ለሚቀጥለው 6 ወራት የሚመራ ቋሚ አስተባባሪ ኮሚቴ ለማስመረጥ በዝግጅት ላይ እንገኛለን፡፡ እስከ አሁን ድረስ ስንቀሳቀስ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አልነበረም፡፡ ከውስጥም ከውጪም የሚያጋጥሙ ችግሮችን በመቋቋም እዚህ ደርሰናል፡፡ አሁን የደረስንበት ሁኔታ ተስፋ ሰጪ ነው፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡- ትብብሩ ስስ ነው፤ ትንሽ ቆይተው አለመግባባት ይፈጥራሉ፤ሁሉም አብረው አይዘልቁም የሚሉ ወገኖች አሉና እርስዎ ምን ይላሉ?

አቶ ግርማ፡- የማራቶን ውድድር አብረው የጀመሩ ሁሉ አይጨርሱም፡፡ እጅግ ውስብስብና ፈታኝ በሆነ ሠላማዊ ትግል አብሮ የጀመረ ሁሉ አብሮ ይጨርሰሳል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ ትግሉ እየጠራና እየገፋ በሄደ ቁጥር እየተራገፈና እየተንጠባጠበ ሊቀር ይችላል፡፡ እስከ አሁን በይፋ ለቅቄአለሁ ብሎ በይፋ መግለጫ የሰጠ ፓርቲ ባይኖርም በተግባር ግን እስአሁን አምስት ድርጅቶች ግንኙነታቸውን አቋርጠዋል፡፡ ነገ ሌላ ሊቀጥል ይችላል፡፡ 15 ወይም 20 ፓርቲ ነጥሮ ቢወጣ አያስገርምም ቁምነገሩ ቁጥሩ ላይ አይደለም ዋናው ቁም ነገር ፓርቲዎቹ ሕዝብና አገር የሚፈልገውን ተግባር እያከናወኑ ናቸው ወይ? የሚለው ነው፡፡ ከህዝብ የሚጠበቀው አመራሩን በቅርብ መከታተለና መቆጣጠር ነው፡፡ ድክመቶችንና ችግሮቹን ብቻ እየነቀሱ በማውጣት መተቸት ሳይሆን እኔንም ያገባኛል ብሎ ከትግሉ መቀላቀል ያስፈልጋል፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡- ህዝብ ዘንድ እንዴት እንደርሳለን? ህዝቡንስ እንዴት ወደ ትግሉ እናስገባለን ብላችሁ ታስባላችሁ?

አቶ ግርማ፡- ኢህአዴግ ተቃዋሚዎች ከህዝብ እንዳይገናኙ የማያደርገው ጥረት የለም፡፡ ህገመንግስቱን ጥሶ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት ፣ሠላማዊ ሠልፍ ማድረግ እየከለከለ ነው፡፡ እኛ ግን መብታችንን ተጠቅመን ትግላችንን እንቀጥላለን፡፡ ዛሬ ሙሉ ለሙሉ በሚባልበት ሁኔታ የሚዲያ አፈና ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ያሉትን ሚዲያዎች ሁሉ እንጠቀማለን፡፡ የኤሌክትሮኒክ ሚዲያዎችን ድህረ ገጾችን በመጠቀም ዓላማችንን እናስተዋውቃለን፡፡ የየፓርቲዎችን መዋቅር እንጠቀምበታን፡፡ የሲቪክስ ማህበራትን መዋቅርም እንዲሁም የመንግስት ሚዲያዎችን እንጠቀማለን ፡፡ በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ እንጠቀማለን፡

ፍኖተ ነፃነት፡- የወቅቱን የአገሪቱን ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት ይገልጹታል?

አቶ ግርማ፡- እንደ 33ቱ ፓርቲዎች በጋራ ገምግመን የደረስንበት ድምዳሜ የለም፡፡ጥያቄህን እንደ ግል የማምንበትን ልመልስልህ፡፡ አገራችን  ከፍተኛ ችግር ውስጥ የወደቀችበት ጊዜው ነው፡፡ አገራችን ዛሬ በማንኪያ የተያዘች፤ ከሥሯ ድንጋይ የሚጠብቃት እንቁላል ሆናለች፡፡ አገራችን በዚያ ድንጋይ ላይ ወድቃ እንዳትከሰከስ ሁላችንም እጃችንን ዘርግተን እንቁላሏን ለማዳን መጠባበቅ አለብን፡፡ የኢህአዴግ እብሪትና

ትዕቢት አገርንና ህዝብን የሚያጠፋ ነው፡፡ የሀገራችን ሁኔታ አሁን ካለበት ወደ ባሰ ደረጃ እየተጓዘ ነው፡፡ ህዝብን እያገለለ ሚዲያን እያፈነ የተለየ ሐሳብ ያለውን ሰው እያጠፋ መጓዝ ይፈልጋል፡፡ ይህ ጉዞ እጅግ አደገኛ ነው፡፡ ህዝቡ ተረድቶታል፡፡ እባካችሁ ተባበሩና ምሩን ሲል ቆይቷል፡፡ እኛም ተባብረናል፡፡ ከእንግዲህ በቁርጠኝነት አገር የማዳን ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡

ፍኖተ ነፃነት፡-አንዳንድ ወገኖች መንግስት በሃይማኖት ውስጥ ጣልቃ እየገባ ነው፣ የተወሰነን ብሔር ለማጥቃት የተነጣጠረ ዘመቻ ጀምሯል ይላሉ፡፡ እርስዎ ምን ይላሉ?

አቶ ግርማ፡- ከጅምሩ የዚህን መንግስት አነሳስ ስንመለከት ገና በረሃ እያለ ዋና ጠላቶች ናቸው ብሎ የፈረጃቸው አሉ፡፡ ከብሔረሰብ አማራን ከሃይማት ኦርቶዶክስን በጠላትነት ፈርጇል፡፡ የብሔር ብሔረሰቦችን ጥያቄ ለመመለስ እነዚህን ሁለቱን ማጥፋት ያስፈልጋል ብሎ አቀደ፡፡ ሁለቱም የአገርና የህዝብ ጠላቶች ናቸው በማለት እንደዓላማ ወይንም እንደ አቅጣጫ አስቀመጠ፡፡ ከተለያየ ቦታ የተገኘ መረጃ የሚያለክተውም ይህንኑ ነው፡፡ገና ትግራይ ውስጥ በነበሩበት ወቅት ከየቤተክርስቲያኑ ካህናትን በማባረር ቤተክርስቲያኖችን በካድሬ ቄሶች እንዲመሩና እንዲተዳደር አድርጓል፡፡ የመንግስት ሥልጣን ከያዙበት ቀን ጀምሮ በአማራውና በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ላይ ሲፈፀም የነበረውን ሁሉ የምናውቀው ነው፡፡ ይህን መናገር ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል፡፡ሰሞኑን በአማራው ህዝብ ላይ እየተፈፀመ ያለውንም ይታወቃል፡፡ በቅርቡ ደግሞ የሃይማኖት ት/ቤታችንን ራሳችንን እናስተዳድር የሃይማኖት መሪዎቻችን እኛን አይወክሉም፤ መጅሊሳችንን ራሳችን እንሰይም፤ አህባሽ የተባለ ባዕድ አስተምሮ ከውጭ አምጥታችሁ አትጫኑብን፤ ብለው በሠላማዊ መንገድ የጠየቁ የተከበሩ የሙስሊሙ የሃይማት አባቶች ላይ እየተፈፀመ ያለውን ድርጊት እየተመለከትን ነው፡፡ የሙስሊሙ ህብረተሰብ ለሠላማዊ ትግል አስተማሪ በሆነና በሠለጠነ መንገድ ተቃውሞአቸውን ሲያሰሙ ቆይተዋል፡፡

መማር ለሚችል ከሙስሊሙ ህብረተሰብ ትግስትና ሠላማዊ ተቃውሞን ተምሯል፡፡ የወያኔ/ኢህአዴግ መንግስት ህዝብን በሃይማኖት ከፋፍሎ ለማፋጀትና ዕድሜውን ለማራዘም ያደረገው ጥረት ከሽፎበታል፡፡ </p><p>የሙስሊሙ ማህበረሰብ አባላት የጠየቁት ጥያቄ መንግስት በሃይማኖታቸው ጣልቃ እንዳይገባባቸው ነው፡፡ ስለዚህ መፍትሔው ከእንግዲህ ሙስሊሙ ክርስቲያኑ መላው የአገሪቱ ህዝብ እጅ ለእጅ ተያይዞ ይህን ሥርዓ ለመቀየር በቁርጠኝነት በጋራ መታገል ነው፡፡----------